# ኢሳት ዶጋ አመድ ይሁን!

ከአቶ ሰውየው በህገሩ (ሰሜን አሜሪካ)

አዎን ኢሳት ዶጋ አመድ ይሁን! እርር ድብን ብትን ይበል! የሀገሬ ሰው ሲተርት የወጋ ሰው ቢረሳ የተወጋ አይረሳም ይላል። ትላንት ሕዝብ የመተረን ፋሺሽት መድረክ የሰጡት ሰዎች ምናልባት የመንግሥቱ ነገር የተረሳ ይመስላቸው ይሆናል። የተበደለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን እንዳ አሁኗ ደቂቃ ጥቃቱን ያስታውሳል። ኢሳት ዶጋ አመድ የሚለውን አባባሌን እንኳን የኢሳት ጭፍን ደጋፊዎች የቅርብ ወዳጆቼንም ያስደነግጣል። ነገር ግን ይህንን ያልኩበትን ምክንያት ላቅርብና ከዚያ በኋላ ሊፈርዱብኝ ይችላሉ።

ሰሞኑን ኢሳት (የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን) ዝግጅት ክፍል በድፍረት መንግሥቱ ኃይለማርያምን ምዕራባውያን በቁሙ ከቀበሩበት መቃብር ቤት አውጥተው ክብር ሰጥተው ያውም "በቀድሞ የኢትዮጵያ ፕሬዝደንትነት" ማዕረግ ከማንዴላ ከዚህ ዓለም በሞት መለየት ጋር አያይዘው ስሙን ለማደስ ያደረጉትን ጥረት ኢትዮጵያውያንን ምን ያክል እንደሚያስቆጣ በቅጡ ያለመረዳት ሳይሆን በእኔ እይታ የማንአለብኝነት የትዕቢትና እብደት ሥራ ነው ባይ ነኝ። ስለሆነም ኢሳት የዶጋ አመድ ይሁን ስል እያንዳንዱን የኢሳት ሚዲያ አመራር ሆነ ደጋፊ ሁሉ በተጠያቂነት ለማስቀመጥ ነው። ከሁሉም በላይ ኢሳት በመላው ዲያስፖራ ታዋቂነት አግኝቷልና በዴሞክራሲ ሙብት ወይም የነፃ ሚዲያ ስም የፈለጉትን ሊተፋብን እንደማይችል መሪ ነን በሚሉን የኢሳት አስተዳዳሪዎች ጭንቅላት ውስጥ እንድሜ ልካቸውን የማይረሱት ሁል ጊዜ በአእምሮአቸው የሚደውል መልዕክት ለማስተላለፍም ጭምር ነው።

በመጀመሪያ ኢሳት የነፃ ሚዲያ አይደለም። ኢሳት የግንቦት ሰባት ንብረት ለመሆኑና የእርዳታ ገንዘብ ምንጩም ከውጪ ኃይል እንደተቆራኘ በቅርቡ ዶ/ር ብርሃኑ ገንዘብ ሲያከፋፍል የነበረበት የቴሌፎን ኮንፈረንስ በየድረ-ገጹ መበተኑ ድሮም በጥርጣሬ ለሚመለከተው ዋና ማስረጃ ስለሆነ ብዙ ነፃ ነፃ ቢሉት ዋጋ የለውም። ኢሳት "የኢትዮጵያ ዲያስፖራ ብቸኛ ጆሮና ዓይን ነው" ብለው እንደሚሰብኩን ሳይሆን በኢትዮጵያዊነት ላይ ስውር አጀንዳ ያለው ለመሆኑ ከብዙ ዝግጅቶቹ አንዱን ከዚህ በታች ያለውን በጊዜው ኢሳት ለማዳፈን ሞክሮ ያልተሳካለትን የአባ ኒቆዲምስን ቃለመጠይቅ ይመልከቱና የራስዎን ፍርድ ይስጡ። በጊዜው በዚህ ቃለ መጠይቅ ላይ የኢሳት ጋዜጠኛ የአነግ ተከላካይ እንጂ ለኢትዮጵያዊነት የቆመ አይመስልም ነበር፤ በጊዜውም እንደኔ ዓይነቱን ብዙ ሀገር ወዳድ አስቆጥቷል።

http://www.youtube.com/watch?v=yYWnEDgTRTY

አለፍ አለፍ ብለው ለምልክትና ለሽፋን ሀገር ወዳድ ወገኖችንና የድርጅት መሪዎችን በመድረካቸው ስላወጡ አጀንዳቸው ኢትዮጵያዊ ነው ብለው የሚገምቱ ካሉ ራሳቸውን ቢጠይቁ መልካም ይመስለኛል።

ኢሳት ግን በኔ ግምት የኢትዮጵያዊነት ማምከኛና የሀገር ወዳድነት ስነልቡና ትጥቅ ማስፈቺያ፤ የዘር ፖለቲከኞች የነኦነግ፣ ኦብነግ፣ የሻእቢያ አተላ ተሸካሚ ጌኛ ለመሆኑ ጥርጥር የለኝም። ስለዚህም ነው ኢሳት ዶጋ አመድ ይሁን! እርር ድብን ብትን ይበል! የምለው። ኢሳት የነጻ ሚዲያ ነው፣ ዴሞክራሲያዊ ምብቱ ነው ብለው ለሚሚግቱኝ ደግሞ ለእኔም ኢሳትን የማውገዝና መራገም መብቴን እንዲያከብሩልኝ በማክበር እጠይቃለሁ።

በሀገራችን በጨካኝነታቸው የሚታወቁ ብዙ ነገሥታት ነበሩን። ለኢትዮጵያዊነት ካበረከቱት ታላቅ ተግባር ጋር ሲመዘን ስማቸው ከእልፈታቸው በኋላ ከፍ ታሪካቸው ተደርጎ ይነገርላቸዋል። ለምሳሌም አፄ ቶዎድሮስን እንውሰድ። አፄ ቶዎድሮስ መቅደላ ላይ የኢቲዮጵያዊነት መሥመርን አሥምረው የከበባቸውን ጠላት አሳፍረው ወገን ቢከዳቸውም የከፈሉት መስዋዕትነት ለትውልድ ህያው አድርጓቸዋል። ወደኋላ አንድ ሁለት ተራራ ቢያፈገፍጉ ማን ይነካቸው ነበር። ነገር ግን የሚመሩት ሕዝብ የማያልፈውን መሥመር በደማቸው ጽፈው ስላስተማሩን ሁላችንም ኢትዮጵያውያን እንኮራባቸዋለን። በነገራችን ላይ በጊዜው የእንግሊዝ ወታደሮች ሲሸሽ ከኋላው ነው የተመታው ለማለት አስከሬናቸውን አገላብጠው እንደ ነበር ይነገራል። ታዲያ ራሱን እንደ አጼ ቶዎድረስ ቆራጥ ተደርጎ እንዲነገርለት ሲያደርግ የነበረው መንግሥቱ ኃይለማርያም ጀግኖች አርዶ፣ አርበኞች አዋርዶ፣ ትውልድ መትሮ፣ ኢትዮጵያን የሚከላከል ወገን አንገት አስደፍቶ ምዕራብያውያን ባቀረቡለት አይሮፐላን በውድቅት ሌሊት ፈርጥጦ ሀገራችንን ለወያኔዎችና ለዛሬ ዘረኞች አስረክቦ የሮጠን ሀገር ከሃዲና ነፍሰ ገዳይ በኢሳት ራዲዮ ድምጹ እንዲሰማ ማድረግን፣ በኢሳት ድረ-ገጽ ላይ ከቃለ መጠይቁ በታች “መንጌ” “መንጌ” ብሎ አስተያየት መደርደሩን ምን አመጣው? ያውም የተቃውሞ ጽሁፎችን እየመረጡ በማውጣት ነፃ ሆኖ ለመታየት የሚደረግ ጥረት ምን የሚሉት ነው? መንግሥቱ ኃይለማርያም ከኢትዮጵያ ሕዝብ ከዘረፈው ገንዘብ አቀመሳቸው እንዴ? ውሻ የበላበት ቤት ይጮኻል ያላሉ አበው። የሻእቢያ ብር ሲቀምሱ ለሻእቢያ ምስክርነት ሲደሰኩሩብን ነበር። የአንዳርጋቸው ጽጌ ኢሳያሳንም ያሽሞነሞነበትን የኢሳት ቃለ መጠይቅ ይመለከቷል።

የኢሳት አዘጋጆች ወይም ኢሳት የነፃ ሚዲያ ነው የሚሉን ወገኖች የደርግ ነፍሰ ገዳዮችና ደጋፊዎች ካልሆኑ በስተቀር ባለንበት የምዕራባውያን ሀገር የነ ሂትለርን ምስል ሆነ አርማ ወይም መጣጥፎችን የሚደግፉና በመልካም ዕይታ እንዲታዮ የሚያደርጉ ላይ በተቃውሞ ከማውገዝ ያለፈ መድረክ የማይሰጧቸው ለምን እንደሆነ ያልተማሩ መሀይማን ናቸው የሚል ግምት የለኝም። ከኢሳት እጠብቅ የነበረው የመንግሥቱን ዓይነት ሀገር ገዳይ ተመልሶ በሀገራችን በሥልጣን ላይ እንዳይወጣ የመንግሥቱን ዕውነተኛ ማንነትና ታሪኩን ማስተማር ሲገባቸው በመድረክ እያቀረቡ የዴሞክራሲ ምብታችን ነው የሚለው ቅዠት አስቀድመው በተረዱት መልካም ነበር። የዴሞክራሲ መብት ነው የሚሉት አነጋገር ከዚህ በፊትም መንግሥቱ እዚሁ በዲያስፖራ ከመካከላችን ባሉ ማረሪያዎች ተረድቶ መጽሐፍ ነው ብሎ ያቀረበው ትፋት በኢንተርኔት ሲበተንበት የዴሞክራሲ መብት ተጣሰ ብለው የጮኹ ክፍሎች አሁንም ተመሳሳይ ጩኸታቸውን ሊያሰሙ ይሞክሩ ይሆናል። ትልባ ቢንጫጫ፣ ይቅናችሁ ነው መልዕክቴ!

ኢሳትን ከልብ የሚደግፉ ሀገር ወዳዶችም እንዳሉ አውቃለሁ። ኢሳት መንግሥቱን በቃለ መጠይቅ ማቅረቡን ካላወገዙ ግን ሀገር ወዳድነታቸው ጥያቄ ውስጥ እንዳይገባ እፈራላቸዋለሁ። ለምሳሌ ታዋቂው ታማኝ ለኢሳት ዋና ገንዘብ አሰባሳቢ ነው። በሀገር ወዳድነቱ ጥያቄ የለኝም። ነገር ግን በኢሳት ደጋፊነቱ ሀገር የገደለን ነፍሰ ገዳይ በኢሳት ለቃለ መጠይቅ መቅረቡን እንዲያወግዝ እጠብቃለሁ። የኢሳት ዝግጅት ክፍልም የመንግሥቱ ኃይለማርያም ሥርዓት የፈጃቸው ኢትዮጵያውያን እስካሁን አጥፍቻለሁ እንኳ ብሎ መናገር ያልቻለን ወንጀለኛ ድምጹን  በራዲዮ እንዲሰሙ በማድረግ በቁስላቸው ጨው መነስነሳቸውን ተረድተው ባስቸኳይ የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ መጠየቅ፣ የቃለ መጠይቁን ቅጂ ከድረ-ገጻቸው ላይ ማውረድ ይጠበቅባቸዋል። ይህን  ውግዘት ደግሞ ከእያንዳንዱ ለኢትዮጵያ ዴሞክራሲ እታገላለሁ ከሚል ግለሰብ፣ ስብስብ፣ ድርጅት ወይም የዲያስፖራ ሚዲያ ሁሉ የምጠብቀው ነው።

ኢሳት ዶጋ አመድ ይሁን! በማለት በዚህ መጣጥፍ ለማሰማት የፈለግኩት፤ መንግሥቱና ግብረ-አበሮቹ ሥልጣኑን ለማጠናከርና ሕዝቡን አንገቱን ለማስደፋት ገና ከጧቱ ሀ ብሎ ከተጠቀመበት ከ60ዎቹ የድሮ መንግሥት ባለሥልጣናትና ተረማጆች ግድያ ጀምሮ የነዚያን ከቤታቸው በራፍ ላይ ተረሽነው የተጣሉና ቤተሰቦቻቸው ወጥተው እንዲዘፍኑ ለተደሪጉ ወንድማማቾች ህጻናት፤  የቀይ ሽብር ሰለባ የሆኑ ኣያሌ ወገኖች፤ አልፎም አስከሬናቸውን ለመውሰድ የጥይት ክፍሉ ተብለው ለተዋከቡ ወገኖቼ፤ በየፋብሪካው በራፍ ላይ ተረሽነው መቀጣጫ እንዲሆን ለተደረጉ የሠራተኛ መሪዎች (ነፍሰ ጡሯን የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ሠራተኞች መሪ የነበረችውን ዳሮ ነጋሽ ሳይቀር)በየበረሃው ተገድለው ለተጣሉ፣ ከአዲስ አባባ ወጣ ብለው በሚገኙ ጣሻዎች ካለፍርድ ተገድለው ተጥለው ወያኔ ለፖለቲካ ፍጆታ ሲል ቆፍሮ ካወጣቸው ወገኖች፤ በየክፍለ ሀገሩ ለተረሸኑ ወገኖች፤ ዛሬም በጊዜው ስየል ተፈጽሞባቸው እያንዳንዷን ደቂቃ የተፈጸመባቸውን በደል የሚያስታውሳቸው የተሰባበረ አጥንት ይዘው እያስታወሱ ተሸክመው በሕይወት ላሉ ወገኖቼና በዝምታ የዛሬውን የመንግሥቱን ቅርሻት በኢሳት አማካይነት እንዲሰሙ ለተገደዱ ሁሉ ድምፅ ልሆንላቸው ብዬ ነው። የመንግሥቱ ኃይለማርያም መንግሥት አንድን የፖለቲካ ፓርቲ ኢሕአፓን ብቻ ሳይሆን የጎዳው ሽብሩ የተነጣጠረው በሁሉ ኢትዮጵያውያን ላይ ነበር። ከራሱ ከደርግ ምክር ቤት አባላት ጀምሮ፣ ከፍተኛ የጦር አበጋዞችን፣ ምሁራንን፣ ተማሪውን ባጠቃላይ ስልጣኑን የተቀናቀኑ የመሰለውን ሁሉ ሲደግፉት የነበሩ የፖለቲካ ስብስቦች አባላትን ሳይቀር አጥቅቷል። ስለሆነም በአሁኑ ጊዜ ኢሳት ያደረገውን ማውገዝ የሁላችንም ተልዕኮ ሊሆን ይገባዋል። አብዛኛው ወገን ዝምታን መምረጡ ለኢሳቶች አይዟችሁ ማለቱ ሳይሆን ስም እንዳይሰጠው ነገር ፈርቶ ዝም ሊል ይችላል። በኔ በኩል ግን ያበጠው ይፈንዳ!  አሁንም ኢሳት ዶጋመድ ይሁን! እርር ድብን ብትን ይበል!

አቶ ሰውየው በሀገሩ  (ከሰሜን አሜሪካ)

ኢሳት ዶጋመድ ይሁን! እርር ድብን ብትን ይበል!

አስመሳይ ሚዲያዎች ይጋለጡ!

ኢትዮጵያዊነት ያለጥርጥር በትግላችን ይለመልማል!